ወጋገን ባንክ

# የፕሬስ መግለጫ

## ወጋገን ባንክ "ከወጋገን ይቀበሉ፣ በወጋገን ይመንዝሩ፣ ይሸለሙ" በሚል ስያሜ ላካሄደው የሎተሪ ዕጣ መርሃ-ግብር አሸፊዎች ሽልማታቸውን አስረከበ

**አዲስ አበባ ፣ ነሐሴ** 15 ቀን 2012 ዓ.ም ፡-ወጋገን ባንክ ከነሐሴ 9 ቀን 2011 ዓ.ም. እስከ የካቲት 3 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ "ከወጋገን ይቀበሉ፣ በወጋገን ይመንዝሩ፣ በወጋገን ይሸለሙ" በሚል ስያሜ ላካሄደው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማበረታቻ ሎተሪ ዕጣ አሸናፊዎች ሽልማታቸውን ዛሬ ነሐሴ 15 ቀን 2012 ዓ.ም የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ኃላፊዎች በተገኙበት በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ባካሄደው ሥነ-ሥርዓት በይፋ አስረከበ፡፡

ከዚህ ቀደም በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አዳራሽ በይፋ በወጣው ዕጣ መሰረት የ1ኛ ዕጣ አንድ ኪያ ስፖርቴጅ የ2019 ሞዴል አውቶሞቢል አሸናፊ በሶማሌ ክልል የቀብሪ ደሃር ከተማ ነዋሪና የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ወጣት ራህማ አብዲ ስትሆን የ2ኛ ዕጣ አምስት የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች አሸናፊዎች ደግሞ የድሬደዋ፣ የባህር ዳር፣ የጅማ፣የሽሬ እና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናቸው ። እንዲሁም የ3ኛ ዕጣ ሃምሳ ስማርት ሞባይል ቀፎዎች አሸፊዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች የሚኖሩ የባንኩ ደንበኞች ናቸው፡፡

ሽልማቱን ለአሸናፊዎች ያስረከቡት የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አባይ መሐሪ እንዳስታወቁት ባንኩ ደንበኞቹን በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ለማሳደግ "ከወጋገን ይቀበሉ፣ በወጋገን ይመንዝሩ፣ በወጋገን ይሸለሙ" በሚል ስያሜ ያካሄደው ይህ የሎተሪ ሽልማት መርሀ-ግብር የባንኩን ደንበኞች ከማሳደግና መልካም ገፅታውን ከመገንባት አንፃር የራሱን በጎ አስተዋፅኦ ማድረጉን ተናግረዋል፡፡

ወጋገን ባንክ በቀጣይም የአሰራ ሥርዓቶቹን በማዘመንና ደንበኛ ተኮር የሆኑ የተለያዩ አዳዲስ አገልግሎቶችን በማቅረብ የደንበኞቹን ፍላጎት ይበልጥ ለማርካት ተግቶ እንደሚሰራ አቶ አባይ መሐሪ ጨምረው ገልፀዋል፡፡ አቶ አባይ በሽልማት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደገለፁት ምንም እንኳን ዕጣው የካቲት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር አዳራሽ በይፋ የወጣ ቢሆንም፣ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት አሸናፊዎችን በአንድ ቦታ አሰባስቦ ሽልማታቸውን ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ባንኩ አብዛኞቹን ሽልማቶች ቀደም ብሎ በዲስትሪክቶች በኩል ለአሸናፊዎች ያስረከበ በመሆኑን በዛሬው ዕለት በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ተገኝተው ሽልማታቸውን የወሰዱት የ1ኛ ዕጣ አሸናፊ፣ አንድ የ2ኛ ዕጣና ሦስት የ3ኛ ዕጣ ዕድለኞች ብቻ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ወጋገን ባንክ በአሁኑ ወቅት በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ 386 ቅርንጫፎቹ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የኤሌክትሮኒክ ባንክ ፡- የኢንተርኔት እና ሞባይል ባንኪንግ አገልግሎቶች ፣ በኤቲኤም እና በክፍያ መፈፀሚያ ማሽኖች የክፍያ ካርድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡እንዲሁም በሁሉም ቅርንጫፎቹ በተለዩ መስኮቶች ወጋገን አማና ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ፤ የደንበኞቹን ፍላጎት በይበልጥ ለማርካት ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ፣ በጅግጅጋ አልበረካ ፣ በአዲስ አበባ አልነጃሺ እና አማና የተሰኙ ቅርንጫፎችን ከፍቶ አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- ማርኬቲንግና ኮርፖሬት ኮሚኒኬሽንስ ዳይሬክቶሬት**
**ስልክ፡- 011 515 5172/ 011 553 9749**